# የኛ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም
# አክሲዮን ማህበር
# የመመስረቻ ጽሁፍ

For Website Use Only

# የኛ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር
# መመስረቻ ጽሁፍ

እኛ ከዚህ በታች ስማችን፣ ዜግነታችን እና አድራሻችን የተገለጸው መሥራች ባለአክሲዮኖች በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 እና በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 ፣ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1164/2012 መስረት ከዚህ በኋላ "ማህበር" እየተባለ የሚጠራው የየኛ ማይክሮ ፋይናንስ አክሲዮን ማህበር መስራቾች በተሻሻለው የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ተስማምተው አፅድቀውታል፡፡

## አንቀጽ 1
## የመሥራች አባላት ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ

የመሥራች ባለአክሲዮኖች ስም ፣ ዜግነትና አድራሻ ከዚህ በታች በተያያዘው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የመሥራች አባላት ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክልል | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቤ.ቁ |
| 1. | ወ/ሮ ፍሬህይወት እሸቱ በቀለ | ኢትዮጵያዊት | አ.አ | ቂርቆስ | 5 | 591 |
| 2. | አቶ እስራኤል አበራ ደምሴ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቂርቆስ | 8 | 279 |
| 3. | አቶ ኤርሚያስ ሙሉጌታ ወንድምሁን | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | የካ | 2 | 2609 |
| 4. | ወ/ሮ ቤተልሔም ተስፋዬ ይመር | ኢትዮጵያዊት | አ.አ | የካ | 10 | 1440 |
| 5. | አቶ ኢሳያስ ለገሰ ነገሬ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | አዲስ | 4 | 116 |
| 6. | አቶ መስፍን ተስፋዬ ይመር | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | የካ | 10 | 1440 |
| 7. | አቶ ኤልያስ አማረ ባይሳ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | የካ | 10 | 2043 |
| 8. | አቶ አብይ ፍስሐ ተ/ዮሀንስ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | የካ | 9 | 709 |
| 9. | ወ/ሪት ሮዛ ተስፋዬ ይመር | ኢትዮጵያዊት | አ.አ | የካ | 10 | 1440 |
| 10. | አቶ ቤዛ ወ/ሚካኤል ዳንጉል | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | የካ | 9 | አዲስ |

For Website Use Only

## አንቀጽ 2

## የማህበሩ ስም፣ የዋና መስሪያ ቤት አድራሻ እና ቅርንጫፎች

1. የማህበሩ ስም "የኛ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር" ተብሎ ይጠራል።
2. የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ነው።
3. ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እንደየ አስፈላጊነቱ ሊከፍት ይችላል።

## አንቀጽ 3
## የአክሲዮን ማህበሩ ዓላማና ተግባር

1. በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራዎች ላይ የተሰማራ የፋይናንስ ተቋም ነው።
2. የውዴታም ሆነ የግዴታ ቁጠባ፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ቁጠባ መቀበል፣
3. በገጠር እና በከተማ በግብርና እና በሌሎች ሥራዎች እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች፣ ዘርፎች ለተሰማሩ ሰዎች የብድር አገልግሎት መስጠት፣
4. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ሰነዶችን ማውጣትና መቀበል፣
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት አነስተኛ የመድን ሥራዎችን መስራት፣
6. ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆኑ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶች እና ሌሎችም የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት መግዛት፣
7. በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ ሥራዎች ወይም በሌሎች ተግባራት ላይ የተሰማሩ የተለያዩ ሰዎች የሚያካሂዷቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ማገዝ፣
8. ለደንበኞች የአመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክሮችን መስጠትና በእነዚህም መስኮች አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ማገዝ፣
9. ለጥቃቅንና ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ወይም መሰል ምርታማ ተግባራት ዓላማ የሚውልን ገንዘብ ማስተዳደር፣
10. የሀገር ውስጥ ሐዋላ አገልግሎት መስጠት፣
11. አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ፋይናንስ ኪራይ አገልግሎቶችን መስጠት፣
12. በዲጂታል ዘዴዎች የተለያዩ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት፣
13. ወኪል ባንኪንግ አገልግሎቶችን መስጠት፣
14. ከወለድ ነጻ አነስተኛ ፋይናንስ ሥራ አገልግሎቶችን መስጠት፣
15. ሥራውን የሚያከናውንባቸው ሕንፃዎችን ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ፣ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፣
16. እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች በሚፈቀዱ ሌሎች የንግድ ስራዎች እና ኢንቨስትመንቶች ላይ መሰማራት።

For Website Use Only

# <u>አንቀጽ 4</u>
# <u>የአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል እና የአክሲዮን ድልድል</u>

1. የማህበሩ የተመዘገበ ካፒታል መጠን ብር160,000,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሚሊዮን ብር) እና የተፈረመ ካፒታል ብር 160,000,000.00(አንድ መቶ ስልሳ ሚሊዮን ብር) ነው፡፡
2. የተፈረመ ካፒታል ነጠላ ዋጋቸው (Par Value) ብር 1,000 (አንድ ሺ ብር) በሆኑ 160,000 አክሲዮኖች ተከፋፍሏል፡፡
3. የተፈረመ ካፒታል ውስጥ ብር 160,000,000.00(አንድ መቶ ስልሳ ሚሊዮን ብር) ተከፍሏል፡፡
4. የማህበሩ አክሲዮኖች ከተጻፈባቸው የአንድ አክሲዮን ነጠላ ዋጋ (Par Value) በሚበልጥ የዋጋ ብልጫ (Premium) ሊወጡ ይችላሉ፡፡
5. ያልተከፈለ የተፈረመ አክሲዮን ካፒታል በሚመለከትም አባላት ለፈረሙት አክሲዮኖች ዋጋ በሙሉ 3(ሶስት) ዓመት ጊዜ ውስጥ የመክፍል ግዴታ አለባቸው፡፡
6. መሥራች አባላት የማህበሩ አጠቃላይ ካፒታል እና አክሲዮን ላይ ያላቸው የተፈረመና የተከፈለ የአክሲዮን ድርሻና የካፒታል መጠን በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ. | የባለአክሲዮኖች ስም | የአንድ አክሲዮን ነጠላዋጋ | የተፈረመ የካፒታል መጠን | የተፈረመ አክሲዮን ብዛት | የተከፈለ ካፒታል መጠን | የተከፈለየ አክሲዮን ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ፍሬህይወት እሸቱ በቀለ | 1,000 | 48,000,000 | 48,000 | 30,152,000.00 | 30,152 |
| 2. | አቶ እስራኤል አበራ ደምሴ | 1,000 | 80,000 | 80 | 20,000.00 | 20 |
| 3. | አቶ ኤርሚያስ ሙሉጌታ ወንድምሁን | 1,000 | 80,000 | 80 | 20,000.00 | 20 |
| 4. | ወ/ሮ ቤተልሔም ተስፋዬ ይመር | 1,000 | 23,400,000 | 23,400 | 23,400,000 | 23,400 |
| 5. | አቶ ኢሳያስ ለገሰ ነገሬ | 1,000 | 24,000,000 | 24,000 | 24,000,000.00 | 24,000 |
| 6. | አቶ መስፍን ተስፋዬ ይመር | 1,000 | 40,000,000 | 40,000 | 26,857,000.00 | 26,857 |
| 7. | አቶ ኤልያስ አማረ ባይሳ | 1,000 | 80,000 | 80 | 20,000.00 | 20 |
| 8. | አቶ አብይ ፍስሐ ተ/ዮሀንስ | 1,000 | 80,000 | 80 | 20,000.00 | 20 |
| 9. | ወ/ሪት ሮዛ ተስፋዬ ይመር | 1,000 | 24,160,000 | 24,160 | 6,138,000.00 | 6,138 |
| 10. | አቶ ቤዛ ወ/ሚካኤል ዳንጉል | 1,000 | 120,000 | 120 | 30,000.00 | 30 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | **160,000,000.00** | **160,000** | **110,657,000.00** | **110,657** |

For Website Use Only

## አንቀጽ 5

## ስለ አክሲዮኖች

1. የማህበሩ አክሲዮኖች በሙሉ እኩል ዋጋ ያላቸው እና በባለአክሲዮኖች ስም የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ናቸው።
2. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምፅ ይኖረዋል።
3. ማህበሩ የትርፍ ድርሻ የሚከፈለው ባለአክሲዮኑ ባለው የተከፈለ የአክሲዮን ዋጋ መጠን ይሆናል።
4. አንድ ባለአክሲዮን በሞት ሲለይ አክሲዮኖቹ ለህጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋሉ።
5. በአክሲዮኖች ላይ ቀሪ ገንዘብ የመክፍል ሃላፊነትን በሚመለከት የንግድ ሕጉ አንቀፅ 289 ተፈፃሚ ይሆናል።
6. ማህበሩ የሚያወጣቸው ሁሉም አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ናቸው። ሆኖም በንግድ ሕጉ መሠረት የማህበሩ አክሲዮኖች ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የጋራ ባለቤት መያዝ የሚችሉ ሲሆን በዚህ መልኩ የማህበሩ አክሲዮኖች በሚያዙበት ጊዜ ባለአክሲዮኖች የጋራ ወኪል የሚሾሙበት አግባብ በንግድ ሕጉ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።
7. የማህበሩ አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ ሲሰጥ በማህበሩ ጉባኤዎች ላይ በመሳተፍ ድምጽ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው። ሆኖም በዚህ ሰነድና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለባለአክሲዮኖች የተሰጠውን የቀዳሚነት መብት የመጠቀም መብቱ ያላቸው ግን የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው።

## አንቀጽ 6
## ስለ አክሲዮን ምስክር ወረቀት

1. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ድርሻቸውን 25% እና ከዛ በላይ ክፍያ ሲፈጽሙ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሲሆን ለዚህ ዓላማ የሚዘጋጀው የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 273 የተገለጹትን ነገሮች ይይዛል፤ ቁጥርም ይሰጠዋል።
2. የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በሙሉ የታተመ ሆነው በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ተፈርመውና ማኅተም ተደርጎባቸው ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ይሰጣሉ።
3. አንድ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ከተበላሸ፣ ከጠፋ፣ ከተሠረቀ ወይም ማንኛውም ዓይነት ጉዳት ቢደርስበት ሕጋዊ መረጃዎችን በማሟላትና የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወስነውን ገንዘብ በማስከፈል በምትኩ ሌላ ምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል።

For Website Use Only

## <u>አንቀጽ 7</u>
## <u>ስለ ባለአክሲዮኖች መብቶች እና ኃላፊነት</u>

1. ባለአክሲዮኖች የሚከተሉት መብቶችና ኃላፊነቶች አሏቸው፡-
   1.1. በማህበሩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል፣ በተወካይ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የመሳተፍና የጉባኤውን ውይይት እና ውሳኔዎች ማወቅ፣
   1.2. በሕግ በተደነገገው መሠረት ካልተገደበ በስተቀር በያዙት የአክሲዮን መጠን ልክ ለጠቅላላ ጉባኤው በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ ድምጽ የመስጠት፣ ለዚህም እያንዳንዱ የማህበሩ አክሲዮን አንድ ድምጽ የመስጠት መብት አለው፣
   1.3. በየሂሳብ ዓመቱ ከተጣራው ዓመታዊ ትርፍና ማህበሩ ሲፈርስ ደግሞ ከሚቀረው የተጣራ ንብረት ላይ በከፈሉት የገንዘብ መጠን ልክ ማግኘት፣
   1.4. ዝርዝር አፈጻጸሙ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እና በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰን ሆኖ አዳዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ ሲቀርቡ ወይም ከነባር ባለአክሲዮኖች የሚተላለፉ አክሲዮኖች ሲኖሩ ባላቸው የአክሲዮን ድርሻ ልክ በቅድሚያ መግዛት፣
   1.5. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤዎች፣ የሂሳብ መግለጫዎችን፣ የትርፍ፣ ኪሳራ መግለጫዎች፣ የተለያዩ ሪፖርቶችን እና ሌሎች የማህበሩን ሰነዶች የማየትና ቅጂዎችን የመውሰድ፤ ሆኖም ተጨማሪ ቅጂዎች የሚሰጡት በማህበሩ የተወሰነው ክፍያ ሲፈጸም ይሆናል፣
   1.6. የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የመምረጥና እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ የመመረጥ እና
   1.7. ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተሰጧቸው መብቶችና ጥቅሞች አሏቸው።
   1.8. በአንቀጽ 8 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አክሲዮን የማስተላለፍ።
2. በሕግ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ባለአክሲዮኖች የሚኖርባቸው ኃላፊነት ለማዋጣት ቃል በገቡት ወይም በፈረሙት የአክሲዮን መጠን ልክ የተገደበ ነው።
3. የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ በመክፈል ላይ የተወሰነ ነው።ሆኖም ወሳኝ ድምጽ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 295 የተመለከተው ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>አንቀጽ 8</u>
## <u>አክሲዮን ስለማስተላለፍ</u>

1. በማህበሩ ውስጥ ያላቸውን የአክሲዮን ድርሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖቻቸውን ማስተላለፍ ሲፈልጉ ሌሎች የማህበሩ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖቹን የመግዛት የቅድሚያ መብት አላቸው።
2. ማንኛውም አክሲዮኖቹን ማስተላለፍ የሚፈልግ ባለአክሲዮን ጥያቄውን አስቀድሞ ለማህበሩ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

For Website Use Only

3. የአክሲዮን ዝውውሩን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል። በመሆኑም የማህበሩ የዳይሬከተሮች ቦርድ የአክሲዮን ዝውውሩ ዝርዝር ጉዳይ የሚፈጸምበትን ቅጽ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት።
4. በአክሲዮን መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማናቸውም ዓይነት የአክሲዮን ዝውውር ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ 9
## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. ማህበሩ በንግድ ሕግ መሠረት የሚዘጋጅና የማህበሩን አክሲዮን የያዙ ባለአክሲዮኖችን ሙሉ ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሟቸውን አክሲዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፣ ከማህበሩ አጠቃላይ ካፒታል አኳያ ባለአክሲዮኖቹ የከፈሉትን የገንዘብና የአክሲዮን መጠን በግልጽ የሚያሳይ የተሟላ መረጃ የሚይዝ የባለአክሲዮኖች መዝገብ በዋና መስሪያ ቤቱ ይይዛል።
2. ማንኛውም ባለአክሲዮን እና በሕግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል መዝገቡን በሥራ ሰዓት ያለ ክፍያ የመመልከት መብት አለው። ሌሎች አካላት በቦርዱ የሚወሰነውን ክፍያ በመፈጸም ሰነዱን መመልከት ይችላሉ።
3. የመዝገቡን ግልባጭ መውሰድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰነውን ክፍያ በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል።

## አንቀጽ 10
## የትርፍ ክፍፍል

1. በሂሳብ ዓመቱ ከተገኘው ገቢ ላይ የማህበሩ ጠቅላላ ወጪዎች፣ ታክስ፣ የአላቂ ንብረት መተኪያ ገንዘብ፣ የእርጅና ቅናሽ እና የተለያዩ በሕግ የሚጠየቁ የመጠባበቂያ ገንዘቦች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪ የሚሆነው ገንዘብ ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ያገኘው የተጣራ ትርፍ ተደርጎ ይወሰዳል።
2. ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው ትርፍ ከሒሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ የቀደምት ዓመታት ኪሣራዎች ካሉ ከተቀነሱ በኋላ በሂሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ በፊት ታስበው ያልተከፋፈሉ ትርፎች እና ሌሎችም ተጨማሪ ገቢዎችን እና በልዩ ሁኔታ ጠቅላላ ጉባኤው ከመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ እንዲከፈል የፈቀደውን ማንኛውንም ገንዘብ በመጨመር የሚገኝ ትርፍ ሲሆን ስለትክክለኛነቱ በማህበሩ የውጭ ኦዲተር መጽደቅ አለበት።
3. የትርፍ ድርሻው ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈልበትን አግባብ በሚመለከት የማህበሩ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚያስተላልፍ ይሆናል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል በሚወስንበት ጊዜ የትርፍ ድርሻው የሚከፈልበትን ሂደት እና የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖች የሚሰጥበትን ቀን በግልጽ ማመልከት ያለበት ሲሆን በዚህ መልኩ የሚሰጠው ጊዜ በማንኛውም መልኩ የትርፍ ድርሻ እንዲከፋፈል ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም።

For Website Use Only

## አንቀጽ11
## የማህበሩ ስራ አመራር አካላት

1. የማህበሩ የአመራር አካላት፡-
    1.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ፣
    1.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
    1.3. ኦዲተሮች፣
    1.4. ዋና ስራ አስፈጻሚ እና ሌሎች የማኔጅመት አባላት፣
    1.5. የማህበሩ ፀሀፊ ናቸው።

## አንቀጽ 12

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የሚሳተፉበት የማህበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ሲሆን አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ በንግድ ሕጉ፣ በሌሎች ሕጎችና እንዲሁም በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።
2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላሉ።
3. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ገዥና ሕጋዊ የሆነ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በንግድ ሕጉ እና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ የተደነገገው ምልዓተ ጉባኤ ሲሟላ እና አብላጫ ድምጽ ሲገኝ ብቻ ነው።
4. ሕግንና የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ በማክበር በተካሄደ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚተላለፍ ውሳኔ ውሳኔውን ከደገፉት ባለአክሲዮኖች በተጨማሪ በጉባኤው ላይ ባልተገኙት፣ በሀሳብ በተለዩ፣ ችሎታ በሌላቸው፣ ድምፀ ተአቅቦ ባደረጉ፣ ድምጽ ባልሰጡና ድምጽ የመስጠት መብታቸው በሕግ በተገደበ ባለአክሲዮኖች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
5. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በውጭ ኦዲተሮች፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በሂሳብ አጣሪዎች፣ በፍርድ ቤት ወይም ሌላ በሕግ የባለአክሲዮኖችን ጠቅላላ ጉባኤን መጥራት እንዲችል ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በኩል የሚጠራ ሲሆን ጥሪ የሚያደርገው አካል የጉባኤውን አጀንዳ የማዘጋጀት ኃላፊነት ይኖርበታል።
6. ከዚህ በላይ በተደነገገው አግባብ ጉባኤው የተጠራው ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውጭ በሆኑ አካላት በሚሆንበት ጊዜ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚሆነው የጉባኤውን ጥሪ ያደረገው ሰው ነው። ነገር ግን ጉባኤውን የጠራው አካል የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሲሆን የቦርዱ ሰብሳቢ የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል። እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ ምክትል ሰብሳቢው የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል።

For Website Use Only

## አንቀጽ 13
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

1. የባለአክሲዮኞች ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ጉባኤው ከሚደረግበት ዕለት ከሃያ አራት ቀናት በፊት አስቀድሞ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሚላክ የተመዘገበ ደብዳቤ፣ በቴሌቪዥን ፣ በሬዲዮ ማስታወቂያ ፣ በኢሜይል መልዕክት ወይም ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ ይደረጋል። የስብሰባ ጥሪው የማህበሩን ስም፣የስብሰባውን ቀንና ቦታ እንዲሁም አጀንዳ መግለጽ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት የተጠራው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይካሄድ የቀረ እንደሆነ ለሁለተኛ ጊዜ የሚደረገው ጥሪ የመጀመሪያው ጉባኤ በተጠራበት አኳኋን እና የጊዜ ገደብ የሚደረግ ሲሆን ጉባኤው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ጊዜ የሚደረገው ጥሪ ከላይ ከተዘረዘሩት የጉባኤ መጥሪያ አማራጮች መካከል በመጠቀም በአንድ ሳምንት ጊዜ ልዩነት ይደረጋል።
3. የጠቅላላ ጉባኤን ለማካሄድ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የጉባኤ ጥሪ ማስታወቂያ በንግድ ሕግ አንቀጽ 371 ስር የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ማካተት ይጠበቅበታል።

## አንቀጽ 14

## የጉባኤው አጀንዳ

1. በንግድ ሕጉ የተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ተወያይቶ ውሳኔ የሚያስተላልፍበትን አጀንዳ ማዘጋጀት ያለበት ጠቅላላ ጉባኤውን የሚጠራው አካል ነው።
2. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ ላይ ያልተካተተ ማንኛውም ጉዳይ ለጉባኤው ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና ውሳኔ ሊተላለፍበት አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመሾምና የመሻር አጀንዳ እንዲሁም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 387(2) መሠረት የሚከናውን ምርጫን ማስፈጸም አስቀድሞ በአጀንዳነት የተያዘ ጉዳይ ባይሆንም በጉባኤው ውይይት ሊደርግበትና ተገቢው ውሳኔ ሊተላለፍበት ይችላል።
4. አስፈላጊው ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ባልተካሄደ ጉባኤ ምትክ በድጋሚ የሚጠራ ጠቅላላ ጉባኤ መወያየት የሚችለው ለመጀመሪያው ጉባኤ በተያዘው አጀንዳ ላይ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 15
## የባለአክሲዮኖች ወኪል

1. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘት ያልቻለ ባለአክሲዮን በንግድ ሕጉ በተደነገገው አግባብ ባለአክሲዮን የሆነም ሆነ ያልሆነ አንድ ወኪል መሾም የሚችል ሲሆን ወኪሉ በጉባኤ ላይ እንዲገኝ ያደረገ ባለአክሲዮን በጉባኤው ላይ በራሱ መሳተፍና ድምጽ መስጠት አይችልም።
2. በዚህ መሠረት ውክልና የሚፈጸምበት የውክልና ስልጣን ቅጽ፣ ይዘት፣ ውክልናው የሚቀመጥበት ቦታና ጊዜ የሚወሰነው በዳይሬክተሮ ቦርድ ሆኖ የጊዜ ገደቡ ግን በማንኛውም መልኩ ጉባኤው ከሚጀመርበት ከ3 ቀናት በፊት መጠናቀቅ አይችልም።

For Website Use Only

3. በጠቅላላ ጉባኤ ለመሳተፍ ባለአክሲዮኖች የሚሰጡት ውክልና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎትም ሆነ በሌላ ስልጣን ባለው አካል የመረጋገጥ ግዴታ የለበትም።

## አንቀጽ 16
## የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ

1. ለእያንዳንዱ ጠቅላላ ጉባኤ ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ላይ መገኘታቸውን የሚያስረዳ የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 378 መሠረትይዘጋጃል።
2. የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በጉባኤው መጀመሪያ ላይ በአካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የፈረሙበት ስለመሆኑ በማህበሩ ፀሀፊ በኩል የሚረጋገጥ ይሆናል።

## አንቀጽ 17
## ስለ ድምጽ ቆጣሪዎች

1. ለጠቅላላ ጉባኤው ድምጽ ቆጣሪ በመሆን የሚያገለግሉ አካላት ፈቃደኛ ከሆኑና በባለአክሲዮንነትም ሆነ በወኪልነት በጠቅላላ ጉባኤው ላይ ከተገኙት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናሉ።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት ድምጽ ቆጣሪ መሆን ያለባቸው ሰዎች ፈቃደኛ ሆነው ካልተገኙ ወይም ደግሞ የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊዎች ሌላ ድምጽ ቆጣሪ የመምረጥ ፍላጎቱ ካላቸው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380(2) ድንጋጌ መሠረት የድምጽ ቆጣሪዎች ምርጫ ጠቅላላ ጉባኤው ሲጀመር የሚከናወን ይሆናል።

## አንቀጽ 18
## ቃለ-ጉባኤዎች

1. የሁሉም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤው ውይይት በቃለ-ጉባኤ ተገልብጦ መያዝ አለበት።
2. ቃለ-ጉባኤው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 387(3) እና (4) ስር የተዘረዘሩትን ዝርዝር ጉዳዮች በመያዝ ሊዘጋጅ የሚገባ ሲሆን ስለትክክለኛነቱ በጉባኤው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ፀሀፊ ተረጋግጦ ሊፈረም ይገባል።
3. የቃለ-ጉባኤው ቅጂዎች ወይም በአጭር የተዘጋጁ ግልባጮች ተቀባይነት የሚኖራቸው በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በጉባኤው ላይ በተገኙ ሁለት የቦርድ አባላት ትክክለኛነታቸው ሲረጋገጥ ነው።

For Website Use Only

# አንቀጽ19
# የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት

1. የሂሳብ ዓመቱ ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ በቀጣይነት ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የማህበሩ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይካሄዳል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበሩ አስፈላጊ በሚሆንበት ማንኛውም ጊዜ ተጨማሪ ሌሎች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤዎችን ሊያካድ ይችላል።
3. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በተለያዩ ሕጎች ከተሰጡት ስልጣኖች በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣኖችና ተግባራት ይኖሩታል።
   - 3.1. የማህበሩን የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ እና የዳይሬክተሮች እና ኦዲተሮች ሪፖርቶችን በማዳመጥ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፣ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማሳለፍ፣
   - 3.2. የዳሬክተሮች ቦርድ አባላትን እና የውጭ ኦዲተሮችን ሹመት ማጽደቅ እንዲሁም ሹመታቸውን መሻርና የሥራ ዋጋቸውን መወሰን፣
   - 3.3. የዳሬከረተሮችን ቁጥር መጨምር ወይም መቀነስ እንዲሁም ዳይሬክተሮች የቦርድ ሥራ የሚለቁበትን ሁኔታ መወሰን፣
   - 3.4. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስንባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ውሳኔ መስጠት።
4. ለመደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊ የሆነው ምልዓተ ጉባኤ የሚሟላው በመጀመሪያው የጉባኤ ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛው ወይም 25% የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው።
5. የጉባኤው ውሳኔ የሚሰጠው ተራ በሆነ የድምጽ ብልጫ ነው። ለድምጽ አቆጣተር ድምጽ ተዐቅቦና ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ካሉ ከግምት ውስጥ አይገባም።
6. የመጀመሪያው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይደረገ የቀረ እንደሆነ ለሁለተኛው ጉባኤ ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸው የአክሲዮኖች መጠን ማናቸውም ቢሆኑ የተገኙት ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነው ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ ጉባኤው ውሳኔ ማሳለፍ ይችላል።
7. ከድምፅ ብልጫ ጋር በተያያዘ የጉባኤው ወሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባኤው ከተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች አብዛኛውን ካፒታል በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፉ ብቻ ነው።

For Website Use Only

# አንቀጽ 20
# አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

1. አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።በስብሰባው ሊታዩ ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ።
   1.1. የማህበሩን የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል፣
   1.2. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፍቃድ ሲያገኝ የማህበሩን ዓላማዎችና ተግባራት ማሻሻል፤
   1.3. የማህበሩን ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ የማሳደግ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ በማግኘት ከአነስተኛ የካፒታል ገደብ ሳያልፍ የማህበሩን ካፒታል መቀነስ፣
   1.4. የማህበሩን ዜግነት መለወጥ፣
   1.5. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ወደ ሌላ ዓይነት ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን እና
   1.6. ሌሎች በሕግ ወይም በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ሰነድ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ጉባኤው ውሳኔዎችን የማስተላለፍ ስልጣን አለው።
2. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊ የሆነው ምልዓተ ጉባኤ የሚሟላው በመጀመሪያው የጉባኤ ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ ሶስተኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው። የመጀመሪያው ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይደረግ የቀረ እንደሆነ በሁለተኛው ጥሪ ድምፅ ለመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው። በሶስተኛው ጥሪ ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸው የአክሲዮኖች መጠን ማናቸውም ቢሆኑ የተገኙት ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነው ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ ጉባኤው ውሳኔ ማሳለፍ ይችላል።
3. ከድምፅ ብልጫ ጋር በተያያዘ የጉባኤው ዉሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባኤው ከተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ሁለት ሶስተኛውን በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፉ ብቻ ነው።
4. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩን ዜግነት የሚለውጥ ውሳኔ የሚተላለፈው ድምጽ የመስጠት መብት ባላቸው ባለአክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ ሲደገፍ ብቻ ሲሆን ነው። እንዲሁም ተጨማሪው ገንዘብ ከማህበሩ መጠባበቂያ ገንዘብ ወይም ሊከፋፈል ከሚችል ትርፍ የሚከፈል ካልሆነ በቀር ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ውስጥ ተጨማሪ መዋዕለነዋይ ከራሳቸው እንዲያፈሱ እና ለዚህም የአክሲዮኖችን ነጠላ ዋጋ ለመጨመር ውሳኔ ለማስተላለፍ የባለአክሲዮኖችን ሙሉ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል።
5. ለድምፅ ብልጫ አቆጣጠር ድምጽ ያልተሰጠባቸውም ሆነ ድምፅ ያልተጻፈባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም።

For Website Use Only

## አንቀጽ 21
## የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. ማህበሩ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በሚሰየሙ እና ቁጥራቸው አምስት በሆኑ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመራል።
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ሲሆን አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ የቦርድ አባላት በድጋሚ በቦርድ አባልነት ሊመረጡ ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ መመረጥ የሚችለው በንግድ ሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተደነገጉትን የብቁነትና ችሎታ መመዘኛዎችን (Qulaification Criteria) ማሟላት ሲችል ብቻ ነው።
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ የስራ ዋጋ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚወሰን ይሆናል።
5. በበጀት ዓመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላት ስራቸውን የተዉ እንደሆነ ቀሪ የቦርድ አባላት በንግድ ሕግ 303(1 እና 2) መሠረት ተተኪ የቦርድ አባል ይሾማሉ።
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪ የቦርድ አባላት ብዛት ከጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከግማሽ በታች ሲሆን ወይም ሁሉም የቦርድ አባላት ሥራቸውን ሲተዉ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 303(3 እስከ 5) ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው እንዲጠራ ተደርጎ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይሾማሉ።

## አንቀጽ 22
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

1. የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በዚህ የመመስረቻ ጹሁፍ እና በማህበሩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሠረት የተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።
2. በንግድ ሕግ አንቀጽ 324 ላይ በተደነገገው መሠረት የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስራቸውን በአንድነት የሚያካሄዱ የማህበሩ እንደራሴዎች ናቸው።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አግባብነት ባላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   - 3.1. በማህበሩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች፣ በንግድ ሕጉ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት የማህበሩን ሥራ እና እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል እንዲሁም ይቆጣጠራል፣
   - 3.2. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔን ሳይተላለፍ የማህበሩን የንግድ እንቅስቃሴ ለማከናውን አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፣
   - 3.3. በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚቀርበውን የማህበሩን ድርጅታዊ መዋቀር፣ ማኔጅመንት ፖሊሲ እና ማኑዋሎች ማጸደቅ፣

For Website Use Only

3.4. የማህበሩን ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሌሎች ተጠሪነታቸው ለቦርዱ የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን መሾም እና/ወይም መሻር ወይም ከስራ ማሰናበት፣ ደሞዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን መወሰን፣

3.5. የማህበሩን ዓመታዊ በጀት እና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ማጸደቅ፣

3.6. የማህበሩን ዋና ገንዘብ መጨመር ወይም መቀነስን በተመለከተ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ጠቅላላ ጉባኤው በሚወስነው መሠረት ተግባራዊ ማድረግ፣

3.7. ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የማህበሩን ሀብት በተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶች ላይ መዋል፣

3.8. የማህበሩን ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት፣

3.9. የትርፍ አመዳደብና የትርፍ ክፍፍልን በተመለከተ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣

3.10. በየሂሳብ ዓመቱ መዝጊያ ማህበሩ ያሉትን ሀብቶች፣ የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫና እንዲሁም የባለፈው ዓመት የማህበሩን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ሪፖርቶችን ለዓመታዊ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

3.11. የማህበሩን ፖሊሲ፣ ፕሮሲጀር፣ ጋይድላይን እና ሌሎች ገዥ የሆኑ ሰነዶችን ማጽደቅ እና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣

3.12. ማህበሩ ብሄራዊ ባንክ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ የብድር ግምገማ ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ

3.13. በማህበሩ ስም ገንዘብ መበደርና እንዲሁም ብድር ለማግኘት እና ዕዳ ለመክፈል የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ የማህበሩን ንብረቶች በዋስትና ማስያዝ፣

3.14. የማህበሩን ዋና ስራ አስፈጻሚ መሾም፣መሻር፣ደሞዝና አበል መወሰን፣

3.15. አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ማህበሩ የሚጠበቅበት የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲያዝ ማድረግ፣

3.16. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባለአክሲዮኖች በወኪል ለመገኘት የሚጠቀሙትን የውክልና ሥልጣን ቅጽ ይዘት፣ ውክልናው የሚቀመጥበትን ቦታና የጊዜ ገደብ ይወስናል፣

3.17. ለማህበሩ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከውጭ ሀገር ወይም ከአገር ውስጥ ባንኮች ገንዘብ ለመበደር የሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብን ማጽደቅ፣

3.18. በማህበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ የሚገባውን የባለአክሲዮኖች መረጃ ምዝገባ ያጸድቃል፣

3.19. የማህበሩን ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለጠቅላላ ጉባኤው ሀሳብ ማቅረብ፣

3.20. ለማህበሩ ገንቢ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ሀሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

3.21. በማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በሚቀርበው ቃለ-ጉባኤ የማህበሩን ቅርንጫፎች መክፈት ወይም መዝጋት፣

3.22. የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መስፈረት የማህበሩን ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚዎችን ፣የውስጥ ኦዲት መምሪያ ፣የሪስክና ኮምፕሊያንስ መምሪያ፣ ምደባና ስንብት ላይ መወሰን፣

For Website Use Only

3.23. በማህበሩ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የስራተኞች ደመወዝ፣የአመታዊ ትርፍ በነስ ስኬላና ጥቅማ ጥቅም ማጽደቅ.፣

3.24. የማህበሩ የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲጸድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

3.25. ማህበሩ ገንዘብ ሲበደር የብድሩን ቅድመ ሁኔታዎች ያጸድቃል እንዲሁም ዋና ሥራ አስፈጻሚው የብድር ስምምነቱን እንዲዋዋል ስልጣን ይሰጣል፣

3.26. የማህበሩን ሂሳብ ስለመክፈት፣ ሂሳቡን ስለማንቀሳቀስ እና የማህበሩን ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በዕዳ ስለሚያዙበት አግባብ የአሰራር ሥነ ሥረዓት በሥራ ላይ ያውላል አሰራሩን ይከታተላል፣

3.27. በማህበሩ ወሳኝ በሆኑ የማህበሩ ኢንቨስትመንት፣ ቋሚ ንብረት እና ቴክኖሎጂ ግዢና ሽያጭ በሚመለከት ውሳኔ መስጠት፣

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቦርዱ ሰብሳቢ እና ዋና ስራ አስፈጻሚ ከባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በአክሲዮን ማህበሩ ስም ብድር ለመበደር ውል እንዲዋዋሉ፡ በብድር ዉል ላይ እንዲፈርሙ፣ የወለድ ምጣኔ ድርድር እንዲያደርጉ እና ብድሩ በአግባቡ ለአክሲዮን ማህበሩ ጥቅም ላይ መዋሉን እንዲከታተሉ እና ለቦርዱ ሪፖርት እንዲያደርጉ፣

5. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቦርድ ስብሳቢ ማንኛውንም ብድር ለማግኘት እና ዕዳ ለመክፈል የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በዋስትና ማስያዝ እና ከሶስተኛ ወገን የሚመጣ ማንኛውንም ብድር በአክሲዮን ማህበሩ ስም ከማንኛውም ባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት መቀበል ወይም መረከብ እንዲችሉ ወይም ጠቅላላ ከሶስተኛ ወገን ይሚምጣን ብድር ለሌላ ህጋዊ አካል ማስተላለፍ እንዲችሉ ፣

6. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቦርድ ስብሳቢ ለአክሲዮን ማህበሩ የሚያስፈልጉ ቋሚ ንብረቶችን እንዲገዙ የተገዙትንም ቋሚ ንብረቶች አስይዘው ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማትና ባንኮች ብድር መበደር እንዲችሉ፣

7. ከባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በአክሲዮን ማህበሩ ስም ከሶስተኛ ወገን የሚመጣን ማንኛውንም ብድር በአክሲዮን ማህበሩ ስም ከባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት መቀበል ወይም መረከብ እንዲችሉ ፣

8. የዳሩክተሮች ቦርድ እጩ ጥቆማና ምርጫ አፈጻጸም መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ወይም እንዲሻሻል ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ማቅረብ፣

9. አስገላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰኑ ስልጣኖቹን በዝርዝርና ግልጸ በሆነመልኩ ለማናቸውም የቦርድ አባል ወይም ለማህበሩ የስራ መሪዎች በውክልና ወይም በቃለ-ጉባኤ መስጠት።

## አንቀጽ 23
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ግዴታና ኃላፊነት

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በሕግ፣ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ እና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የተጣለባቸውን ኃላፊነቶችና ግዴታዎች በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ ከአንድ ወኪል በሚጠበቅ ጥንቃቄና ትጋት ተግባራቸውን መፈጸም ይኖርባቸዋል። ዳይሬክተሮች በዚህ አግባብ የተጣለባቸውን ግዴታ ያጓደሉ እንደሆነ ለሚደርሰው ጉዳት ለማህበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ። እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለማህበሩ፣ ለሶስተኛ ወገኖች፣ ለባለአክሲዮኖች እና ከማህበሩ ላይ ገንዘብ ለሚጠይቁ ሶስተኛ

For Website Use Only

ወገኖች በሚኖርባቸው ተጠያቂነት ላይ አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕግ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ተፋጻሚ የሚደረጉ ይሆናል።

2. ከማህበሩ ሥራ ጋር በተያያዘ በቸልተኝነት፣ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወይም በእምነት ማጉደል ምክንያት ሊደርስበት ከሚችል ተጠያቂነት አንድን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነጻ ለማድረግ ታስቦ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ስምምነት ወይም ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
3. አንድ የቦርድ አባል የወሰነው ውሳኔና የሰራው ስራ የጠቅላላ ጉባኤን ውሳኔ፣ የዚህን መመስረቻ ጽሁፍ ድንጋጌዎችና ሕግን የተከተለ እንደሆነ ውሳኔውና ሥራው ማህበሩ ላይ ላደረሰው ጉዳት የቦርድ አባሉ ተጠያቂ አይሆንም።

## <u>አንቀጽ 24</u>
## <u>የዳይሬክተሮች ምርጫና የዋስትና አክሲዮን</u>

1. ዳይሬክተሮች ለሶስት ዓመት ጊዜ ለማገልገል ይመረጣሉ።
2. ዳይሬክተሮች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት በሥራ ዘመናቸው መጨረሻ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ።
3. የቦርዱን ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ጠቅላላ ጉባኤው የተወሰኑትን ዳይሬክተሮች ቦርዱ አባላት ለሶስተኛ ጊዜ ሊመርጡ ይችላሉ። ሆኖም ለሶስተኛ ጊዜ የሚመረጡት የዳይሬተሮች ቦርዱ አባላት ቁጥር ከጠቅላላ የቦርዱ አባላቱ አንድ ሶስተኛ አይበልጥም።
4. ዳይሬክተሮች ከመካከላቸው አንድ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣሉ።
5. የቦርዱ ሊቀመንበር የቦርዱን ሰብሰባዎች ይመራል፣ እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበር ስብሰባውን ይመራል፣ ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው የሚመረጡው ዳሬክተር ስብሰባውን ይመራል።
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በመሆን የሚመረጡ ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ውሰጥ ካላቸው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ 10 በመቶኛ የሚሆነውን አክሲዮን የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በማድረግ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
7. በቦርድ አባልነት የሚመረጡት ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች በሚሆኑበት ጊዜ 40 በመቶኛ ዋስትና ለማህበሩ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በዚህ አግባብ የሚቀርበው ዋስትና በማህበሩ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይገባል።
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያስይዙት የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ለዳይሬክተሮች የሚለቀቀው በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ከማህበሩ የሚፈለግባቸው ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

For Website Use Only

## አንቀጽ 25
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. ቦርዱ ስብሰባውን የሚያካሂደው በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም እሱ በሚወስነው በማንኛውም ሌላ ቦታ ሊሆን ይችላል።
2. የቦርዱ ስብሰባዎች የሚጠሩት በሊቀመንበሩ ሲሆን እርሱ በማይኖርበት ጊዜ በምክትሉ ይጠራሉ። የስብሰባ ጥሪውም አጀንዳውን የሚገልጽ ሆኖ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ለዲሬክተሮች በሙሉ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ሁሉም የቦርድ ስብሰባዎች የሚመሩት በቦርዱ ሊቀመንበር ሲሆን እርሱ በሌለበት ጊዜ በምክትሉ ይመራሉ።
3. በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ማንኛውም ዓይነት ውሳኔ የሚተላለፈው ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ዳይሬክተሮች በስብሰባው ላይ ሲገኙ ብቻ ነው።
4. በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባ ላይ በተለያዩ መንገድ ከተገኙት መካከል በድምጽ ብልጫ ሲገደፍ ነው። ድምጽ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርድ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል።ዲያሬክተሮች የራሳቸውን ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት ጉዳዮች ድምጽ መስጠት አይችልም።
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በቦርድ ስብሰባ ላይ ቪዲዮን ጨምሮ በሌላ ለሰብሰባ ምቹ በሆነ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መሳተፍ ይችላሉ። ይህ የመገናኛ ዘዴ የተሰብሳቢዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል፣ ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ፣ የተሳታፊዎችን ድምጽ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ከጠቅላላ የቦርድ አባላት መካከል ቢያንስ አንድ ሶስተኛው በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በስተቀር የቦርድ አባላት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በተሳተፉበት ስብሰባ ላይ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም።
7. አንድ የቦርድ አባል በስበሰባው ላይ መወከል የሚችለው በሌላ የቦርድ አባል ብቻ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ በላይ የቦርድ አባላትን መወከል አይችልም።
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባኤ መመዝገብ እና በስብሰባው በተገኙና በተወከሉ ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ፀሀፊ መፈረም ይኖርበታል።
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቦርድ ስብሰባዎች የሚመሩበትን ዝርዝር የሥነ ሥርዓት ደንብ በማውጣት በስራ ላይ ያውላል። ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ውስጥ ደንቡ በዋነኛነት ስብሰባዎቹ የሚደረጉበትን ጊዜ፣ ስብሰባዎቹ የሚደረግበትን ቦታ እንዲሁም ጥሪ የሚደረግበትን መንገድ ይይዛል።

For Website Use Only

## አንቀጽ26
## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ሹመት ስለመሻር

ያለ በቂ ምክንያት ከቦርድ አባልነቱ የተነሳ የቦርድ አባል አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላትን ሹመት በማናቸውም ጊዜ የመሻር ሙሉ ስልጣን አለው።

## አንቀጽ 27
## የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

1. ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾምና የማህበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በዋና ኃላፊነት የሚመራ አንድ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚኖረው ሲሆን የዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪነት ለማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይሆናል።
2. ዋና ሥራ አስፈጻሚው የማህበሩ ተቀጣሪ ሲሆን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በተመሳሳይ ሰዓት የማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢ መሆን አይችልም።
3. ማህበሩ በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት የዳይሬክተሮች ቦርዱ የሚሾማቸው ከአንድ በላይ ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚዎች ወይም ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ሊኖሩት ይችላሉ።
4. ዋና ስራ አስፈጻሚው የሚሾመው፣ ደመወዝና የአገልግሎት ጊዜውም የሚወሰነው በዳይሬክተሮች ቦርዱ ይሆናል።
5. የዋና ስራ አስፈጻሚው ተግባርና ስልጣን በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ እና አግባብነት ባለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ ላይ እንደተወሰነው ይሆናል።

## አንቀጽ 28
## የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣንና ተግባር

ዋና ሥራ አስፈጻሚው በንግድ ሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ መመሥረቻ ጽሁፉ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ላይ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በኩል በሚሰጠው ውክልና መሠረት ማህበሩን በሶስተኛ ወገኖች ፊት ይወክላል፣
2. የማህበሩን ጠቅላላ እንቅስቃሴዎች አስቀድሞ ያቅዳል ለቦርዱ አቅርቦ ያጸድቃል ያስፈጽማል፣
3. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚያጸድቃቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ዓመታዊ ዕቅዶች፣ የአሠራር ማኑዋሎች፣ ዓመታዊ በጀት እና ውስጠ ደንቦችን በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደረጋል፣
4. የማህበሩን አላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን ሁሉ በማህበሩ ስም መስራት፣የማህበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ አንቅስቃሴዎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል እና ያስተዳድራል፣

For Website Use Only

5. በማህበሩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እና በዳይሬክቶሮች ቦርድ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በሥራ ላይ ያውላል፣
6. የማህበሩን ጥቅም ለማስጠበቅ ወኪሎችን፣ የሕግ ባለሙያዎችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን ይሾማል ወይም ይሽራል፣
7. ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት በማህበሩ ስም የማህበሩን ሂሳቦችን ያስተዳድራል፣
8. መመስረቻ ጽሁፉን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻያ ሀሳብን የዳይሬክተሮች ቦርድ ተወያይቶበት ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ እንዲችል ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፣
9. የማህበሩን የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ በማዘጋጀት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፣
10. በተለያዩ ተቋማት ዘንድ ማህበሩን ወክሎ በመቅረብ ጉዳዮችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል ወይም የማህበሩን ሌሎች ባለሞያዎችን ይወክላል፣
11. የማህበሩን የውስጥ ኦዲት መምሪያን እና የማህበሩ ፀሀፊ ሹመት፣ ምደባና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ማስወሰን፣
12. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ ሰነድ የተሰጡትን ስልጣንና ኃላፊነቶች እንደ ሁኔታ ለሚመለከተው የማህበሩ ሠራተኛ ወይም ለሌሎች ባለሙያዎች በውክልና ይሰጣል፣
13. የማህበሩን ወኪል ወይም ሰራተኛ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን፣ ደሞዙን ጉርሻና ሌሎች ከመቀጠርና ከስንብት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ተቋሙ ባለው አሰራር መሠረት ይወስናል፣
14. ማህበሩን ተከራካሪ ወገን በሆነባቸው የፍርድ ቤት ጉዳዮች ማህበሩን በመወከል አስፈላጊውን ይፈጽማል። የሕግ ባለሞያ በመቅጠር ወይም በመወከል የማህበሩን ጥቅም ያስከብራል፣
15. በማህበሩ ስም በባንክ ወይም ባንኮች የባንክ ሂሳብ መክፈትና ማንቀሳቀስ፣
16. በማህበሩ ስም ቼክ፣ የሚተላለፍ ሰነዶች፣ እንደ የሃዋላ ወረቀት ያሉ የንግድ ሰነዶችን ማውጣት፣ መፈረም፣ መቀበል፣ ማስተላለፍ እንዲሁም መመንዘር ይችላል፣
17. በቦርዱ የሚሾሙ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን ዕጬ ለቦርዱ አስቀርቦ ሹመታቸውን ያስጸድቃል፣
18. ቅርንጫፎች እንዲከፈቱ ወይም እንዲዘጉ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣
19. የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች ለዳሬክተሮች ቦርድ ማቅረብ፣
20. የማህበሩን የኢንቨስትመንት ዕቅድና አማራጮችን በማዘጋጀት ለቦርዱ ማቅረብ፣
21. የማህበሩን እስትራቴጂዊችን ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ማቅረብ፣
22. የማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር ማዘጋጀት፣ በቦርዱ ሲጸድቅ ስራ ላይ ማዋል፣
23. በዳይሬክተሮች ቦርድ ሊሰጡ የሚችሉትን ሌሎች ሥልጣናትና ግዴታዎች መፈጸም፣
24. ማህበሩ ከፎርክሎዠር ጋር በተያያዘ የተረከባቸውን ንብረቶች፣ ጉዳት የደረሰባቸው ወይም በእርጅና ምክንያት መወገድ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎችን ሌሎች ንብረቶች እንዲሁም ከማህበሩ መደበኛ ስራ ጋር በተገናኘ ሌሎች የማህበሩ የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን እንዲሸጡ፣ እንዲወገዱ መወሰን፣
25. የሂሳብ ዓመቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከሁለት ወር በፊት የማህበሩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ማዘጋጀትና ቦርድ እንዲያጸድቁው ማቅረብ፣
26. የሥራ ክንውን ሪፖርት በየሰስት ወሩና የሂሳብ ሪፖርት በየዓመቱ ለቦርዱ ማቅረብ፣

For Website Use Only

27. ከተሰጡት ሀላፊነቶች መካከል ለሌሎች የማህበሩ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች በውክልና ማስተላለፍ፣

28. በአክሲዮን ማህበሩ ስም ከባንኮችና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ከሶስትኛ ወገን የሚመጣን ማንኛውንም ብድር በአክሲዮን ማህበሩ ስም መቀበል ወይም መረከብ እንዲችሉ

29. ከማህበሩ ስራ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም የንግድ ልውውጦችን በተመለከተ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውል ይዋዋላል፣ማህበሩን በመወከል ይፈርማል፣

30. ከዳይሬክተሮች ቦርድ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት በማህበሩ ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል፣ ከማህበሩ የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ ንብረቶችን ይሸጣል፣ በማህበሩ ስም ማንኛውንም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት መከራየትም ሆነ ማከራየት፣ የአከራይም ሆነ የተከራይ ውል መፈጸም፣ ውል ማደስ፣ ውል ማሻሻል እና ውል ማፍረስ ይችላል።

## አንቀጽ 29
## የማህበሩ ፀሀፊ

1. ማህበሩ በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በኩል የሚቀጠርና የሚሰናበት የማህበሩ ተቀጣሪ የሆነ ፀሀፊ ይኖረዋል።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ1 መሠረት የሚሾመው የማህበሩ ፀሀፊ ተጠሪነቱ ለማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል።
3. የማህበሩ ፀሀፊ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የተጣሉበት ስልጣንና ኃላፊነቶች ሁሉ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን በያዙ ቃለ-ጉባኤዎችና የቃለ-ጉባኤዎች ቅጂ ላይ የመፈረም፣
   ለ. የማህበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፣
   ሐ. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፣
   መ. ቃለ-ጉባኤዎችን የማዘጋጀትና የማደራጀትና
   ሠ. እንዲሁም ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚዘጋጁ የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዘገቢያ ሰነዶች ላይ የጉባኤው ተሳታፊ ባለአክሲዮኖች እና ተወካዮቻቸው በትክክል የፈረሙ መሆኑን ማረጋገጥ።
4. የማህበሩ ፀሀፊ የሕግና የዚህን መመስረቻ ጽሁፍ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በማህበሩ፣ በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ ነው።

## አንቀጽ 30
## የውጭ ኦዲተሮች

1. ማህበሩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚሾሙ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የውጭ ኦዲተሮች ሊኖሩት ይችላሉ። የውጭ ኦዲተሮች የሥራ ዋጋ ሹመታቸውን በሚያጸድቀው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚወሰን ይሆናል።

For Website Use Only

2. ያለ በቂ ምክንያት ሹመቱ የተሻረበት የውጭ ኦዲተር ለደረሰበት ጉዳት የጉዳት ካሳ ጥያቄ የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ጊዜ የውጭ ኦዲተሮችን ሹመት የመሻር ስልጣን አለው።
3. ከዚህ በላይ በተደነገገው አግባብ የማህበሩ የውጭ ኦዲተር ከኃላፊነቱ በሚነሳበት ጊዜ ማህበሩ የውጭ ኦዲተሩ ከኃላፊነቱ የተነሳበትን ምክንያት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል።
4. የማህበሩ የውጭ ኦዲተር በመሆን ማገለግል የሚችሉት በንግድ ሕጉ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሌሎችም አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተደነገጉትን የብቁነት መሥፈርቶች የሚያሟሉ የውጭ ኦዲተሮች ብቻ ናቸው።
5. ለማህበሩ የሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች የአገልግሎት ዘመን ለተከታታይ ሶስት ዓመት ይሆናል።
6. የውጭ ኦዲተሩ ስልጣን፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት በንግድ ሕግ ከአንቀጽ 345 እስከ 355 ባሉት ድንጋጌዎችና፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚገዛ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል።
   ሀ. ስራውን ለማከናወን አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን የማህበሩን መዛግብትና ሰነዶችን መመርመር፣ የማህበሩን ንብረት፣ ሂሳብ ማመዛዘኛ ትርፍና ኪሳራውንም የሚያሳዩትን መዛግብት ትክክለኝነት ማረጋገጥ፣
   ለ. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሰጠው ሪፖርት ትክክለኛ እና የማህበሩን እውነተኛ ገጽታ የሚያሳይ መሆኑን ማረጋገጥ እና ሪፖርቱን ለሚያጸድቀው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በንግድ ሕጉ መሠረት አስተየየት መስጠት፣
   ሐ. ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤን ጨምሮ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ የመሳተፍ፣
   መ. የንግድ ሕጉን ጨምሮ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ በተደነገገው አግባብ የማህበሩን ባለአክሲዮኞች ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት እና
   ሠ. የዓመቱ የሂሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የኦዲት ሪፖርቱ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መላክ አለበት።

## <u>አንቀጽ 31</u>
## <u>ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፤ ይሁንና ማህበሩ በንግድ ሕግ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ላይ በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በማናቸውም ጊዜ ሊፈርስ ይችላል።

## <u>አንቀጽ 32</u>
## <u>ሪፖርት</u>

1. ማህበሩ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ 30ቀናት ውስጥ የፋይናንስ መግለጫዎችን እና የስራ ሪፖርቶችን በማህበሩ ድህረገጽ ላይ በማውጣት በቂ መረጃ ለህዝብ እንዲደርስ ያደርጋል።
2. ማህበሩ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች እና ሌሎች ሕጎች ላይ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ እነዚህን ሪፖርቶች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይልካል።

For Website Use Only

## **አንቀጽ 33**
## **የማህበሩ የሂሳብ ዓመት**

የማህበሩ የሂሳብ ዓመት የሚጀምረው እ.ኤ.አ ጁላይ 1 ቀን ሆኖ በቀጣዩ ዓመት ጁን 30 ቀን ያበቃል።

## **አንቀጽ 34**
## **ሕጋዊ መጠባበቂያ**

1. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 434 መሠረት ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ በየዓመቱ 5% ለህጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ይቀነሳል፤ ይህም የሚሆነው ሕጋዊ የሆነው የመጠባበቂያ ገንዘብ የማህበሩን ዋና ገንዘብ 5% እስኪደርስ ነው።
2. ከዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ከማንኛውም ኦዲተር ሃሳብ የቀረበለት እንደሆነ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ተጨማሪ ወይም አማራጭ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲኖር መወሰን ይችላል።

## **አንቀጽ 35**
## **የማህበሩን ዋና ገንዘብ መጨመር**

**1.** የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ የሚቻለው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሲፈቅድ ብቻ ነው፡ ፡ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ዋና ገንዘቡ የሚያድግበትንም መንገድ አብሮ መወሰን ይኖርበታል።
**2.** አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩን ካፒታል ለማሳደግ የሰጠውን ውሳኔ ተግባራዊ እንዲያደርግ አስፈላጊውን ስልጣን ለማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ መስጠት ይችላል።
**3.** የማህበሩን ዋና ገንዘብ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ወይም የነባር አክሲዮኖችን ዋጋ በመጨመር ማሳደግ ይቻላል።
**4.** የአዲስ አክሲዮኖች ዋጋ በሚከተሉት መንገዶች ሊከፈል ይችላል።
ሀ. በጥሬ ገንዘብ ወይም አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔረዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በዓይነት እና
ለ. መጠባበቂያ ወይም ማህበሩ ሊያዝባቸው የሚችሉ ሌሎች ገንዘቦችን ወደ ዋናው ገንዘብ በመጨመር ነው።
**5.** አስቀድሞ የተፈረመው የማህበሩ ዋና ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅካል ተከፈለ በስተቀር በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ዋና ገንዘቡን ማሳደግ አይቻልም።

## **አንቀጽ 36**
## **የፋይናንስ ሪፖርት፣ መዝገባዎች እና መረጃ**

For Website Use Only

1. ማህበሩ የሚገኝበትን ደረጃ በግልጽና በትክክል የሚያሳዩ እንደሁም የተቋሙን የንግድ ልውውጦችና የፋይናንስ አቋም የሚያሳይ የፋይናንስ ምዝገባዎችን እና መረጃዎችን አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።
2. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማህበሩን ጠቅላላ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት፣ የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ እና ሌሎች በሕግ የሚጠየቁ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል እንዲሁም በጋዜጦች ላይ በማሳተም እና በማህበሩ ድህረ-ገጽ ላይ በመጫን ህዝቡ እንዲያውቀው ያደረጋል።

## አንቀጽ 37
## የማህበሩ ድህረ-ገጽ

1. በንግድ ሕግ አንቀጽ 492 ላይ በአክሲዮን ማህበራት ላይ በተጣለው ግዴታ መሠረት ማህበሩ ለማንኛውም ሰው ተደራሽ የሚሆን የራሱ ድህረ-ገጽ ይኖረዋል።
2. በማህበሩ ድህረ-ገጹ ላይ የሚገለጹ ጉዳቶችንና እንዲሁም በዚህ መልኩ የተጫኑ መረጃዎች በድረ-ገጹ ላይ የሚቆዩበትን ጊዜ በሚመለከት በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈጻሚ የሚደረጉ ይሆናል።
3. ማህበሩ የድረ-ገጹን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያስችለው አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል።

## አንቀጽ 38
## ባለአክሲዮኖች ከማህበሩና ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት

የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ከማህበሩ እና ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በዋነኛነት በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ አግባብነት ባላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እና በዚህ ጉዳይ ዙሪያ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚገዛ ይሆናል።

For Website Use Only

## አንቀጽ 39

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ የአማርኛ እና የእንግሊዘኛ ቅጂዎች መካከል የትርጉም ተቃርኖ ወይም ማንኛውም ዓይነት ግጭት ሲፈጠር የሰነዱ የአማርኛው ቅጂ ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል።
2. የመመስረቻ ጽሁፉ ሰነድ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ብቻ ነው። በዚህ አግባብ የተሻሻለው ሰነድ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ መጽደቅ እና በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት መረጋገጥና መመዝገብ ይኖርበታል።
3. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ሰነድ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የንግድ ሕጉ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1164/2012 ፣የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና ሌሎችም አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ይህን የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ በአዲስ አበባ ከተማ በሚያዚያ 04 ቀን 2016 ዓ.ም አንብበው በፊርማቸው አጽድቀዉታል።

| ተ.ቁ. | የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም | ፊርማ | የተወካይ ስም |
|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ፍሬህይወት እሸቱ በቀለ | | |
| 2. | አቶ እስራኤል አበራ ደምሴ | | |
| 3. | አቶ ኤርሚያስ ሙሉጌታ ወንድምሁን | | |
| 4. | ወ/ሮ ቤተልሔም ተስፋዬ ይመር | | |
| 5. | አቶ ኢሳያስ ለገሰ ነገሬ | | |
| 6. | አቶ መስፍን ተስፋዬ ይመር | | |
| 7. | አቶ ኤልያስ አማረ ባይሳ | | |

For Website Use Only

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8. | አቶ አብይ ፍስሐ ተ/ዮሀንስ | | |
| 9. | ወ/ሪት ሮዛ ተስፋዬ ይመር | | |
| 10. | አቶ ቤዛ ወ/ሚካኤል ዓንጉል | | |

For Website Use Only